**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

# እውነት ሲገለጥ፤ ሥልጣን ሲሸረሸር!

ስለ እውነት ብዙ ተጽፏል፤ ብዙም ተብሏል፡፡ የተባለውን ያህል ቢሆንም ግን እውነትን የሚወዱት ያሉትን ያህል የሚፈሯትና ከቻሉም ለማጥፋት የሚመኙት ጥቂት አይደሉም፡፡ በተለይ አምባገነኖች በዚህ ጉዳይ ቀዳሚ ተጠቃሾቸ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያም ያለው ይህ እውነትን የሚፈራ አገዛዝ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለሐቅ፣ ለእውነት የቆሙትንና ሕዝብ ይህንን እውነት እንዲያውቅ ያለመታከት እየሰሩ ያሉትን ጋዜጠኞች ማሳደዱንና ማሰሩን ቀጥሎበታል፡፡ የዚህ ድርጊት ዋንኛው ምክንያት ፍርሃት ነው፡፡ የፍርሐቱ መስመር መልቀቅ ደግሞ ብዕር ይዘው ስለእውነት የሚፋለሙትን ጋዜጠኞች ቦምብ እንደታጠቁ አሸባሪዎች ተከስሰው ለእስር ዳርጓቸዋል፡፡

ሲጀመር የጋዜጠኛነት ሙያ አሸባሪ ተባለ፡፡ ከዚያም ጋዜጠኞች መታደን ጀመሩ፡፡ **ውብሸት ታዬ** የአውራምባ ታይምስ ምክትል ዋና አዘጋጅ በተያዘ በሁለተኛው ቀን የፍትሕ ጋዜጣ ዘጋቢ **ርዕዮት ዓለሙ** ወደ ማዕከላዊ እስር ቤት ተወሰደች፡፡ ከእነዚህ ጋዜጠኞች ሌላ 7 ግለሰቦችም ታስረዋል፡፡የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊ/መ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር እና የፓርቲው አባል ደጀኔ ተፈራ ወደ እስር ወረዱ - ሁሉም የተከሰሱት አዲስ በወጣው የጸረ-አሸባሪነት ሕግ ነው፡፡

ሕወሃት/ኢህአዴግ የፈለገውን ሕግ እያወጣ ያሻውን በዜጎች ለመፈጸም ቢፈልግም እውነትን ግን ለዘላለም ማፈን አይችልም፡፡ **እኛም ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ውስጥ የምንገኝ በሙሉ ይህንን በአሸባሪነት ስም በዜጎቻችን ላይ የተካሄደውን ሕገወጥ ተግባር አጥብቀን እያወገዝን የታሰሩት በሙሉ ባስቸኳይ እንዲለቀቁ አጥብቀን እናሳስባለን፡፡** ይህንን የምንለው ለይስሙላ ወይም መባል ስላለበት እንዳልሆነ ሁሉም ወገን እንዲረዳልን እንወዳለን፡፡ ስለሆነም በእነዚህም ሆነ በሌሎች ዜጎቻችን ላይ የሚፈጸመው በደል በሙሉ በአቶ መለስ ለብቻ የሚካሄድ ባለመሆኑ ከላይ ጀምሮ በተዋረድ ይህንን ኢሰብዓዊ ተግባር በሚፈጽሙት ሁሉ የጋራ ንቅናቄያችን መረጃ እንደሚያሰባስብና ወቅቱን ጠብቆ ለፍርድ እንደሚያቀርባቸው ጭምር ልናሳስብ እንወዳለን፡፡

ይህ በጋዜጠኞች ላይ እየተካሄደ የመጣው አፈና ከዚህ በፊት በሌላ መልኩ በሌሎች ላይ ሲካሄድ ነበር፡፡ በሰሜን አፍሪካ የለውጥ ማዕበል እየተቀጣጠለ በሄደበት ጊዜ ህወሃት/ኢህአዴግ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የኦሮሞ ተወላጆች ወደ እስር ቤት ሲያጉር ሰንብቶ ነበር፡፡ ሆኖም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተፈጠረውን ስንመለከት የዋጋ ግሽበት ከመጠን በላይ ከመናር አልፎ በአሁኑ ጊዜ ገንዘብ ያለው እንኳን በገንዘቡ ለመግዛት የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ የኢሣት ቴሌቪዥን እንዲሁም የአሜሪካና የጀርመን ድምጽ ራዲዮኖችን የመሸበብ ተግባሩ ባያሌው በርትቷል፡፡ የመሬት ነጠቃው፣ ነዋሪዎችን ከቀያቸው የማፈናቀል ተግባር፣ የስለላው መረብ በነፍስ ወከፍ ደረጃ መስፋፋት፣ አሁን ደግሞ በአሸባሪነት ሰበብ የሚዲያ ሰዎች ላይ እየተካሄደ ያለው ዘመቻ የአገዛዙ የፍርሃት መጠን ምንያህል እያደገ መምጣቱን በጉልህ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከምዕራባውያን በኩል ያለው ድጋፍም ከተሸረሸረ ሰንብቷል፡፡ በተለይም ሂላሪ ክሊንተን አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ የተከሰተውን መመልከቱ ብቻ በቂ ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡

የአቶ መለስ አገዛዝ በአገር ውስጥና በውጪ እየደረሰ ያለበትን ተቃውሞ ለማለዘብ አሁንም መፍጨርጨሩን አላቆመም፡፡ ለዚህም ነው ሰሞኑን ‹‹ሠራዊቱን ሕብረብሔራዊ አደረጃጀት እንዲኖረው›› በሚል ሰበብ የጦር መኮንኖችን አባርሬአለሁ እያለ የሚደሰኩረው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ በየቦታው ያሰማራቸው ካድሬዎች አሁንም በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የአገዛዙን ‹‹መልካምነት›› እና ‹‹ዴሞክራሲያዊነት›› ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እየሰበኩ ይገኛሉ፡፡

የጋራ ንቅናቄያችን ዋና ዳይሬክተር አቶ ኦባንግ የጀርመን ድምጽ ራዲዮ በቦን ከተማ ባዘጋጀው ዓለምአቀፍ የሚዲያና የሰብዓዊ መብት ጉባዔ ላይ ተገኝተው በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው አጠቃላይ የመብት ረገጣ፣ አፈና፣ እስራት፣ ግድያ ወዘተ ሰፋ ያለ ንግግር አድርገው ነበር፡፡ ከንግግሩ በኋላ በተካሄደው የፓናል ውይይት ለስብሰባው ከአዲስአበባ ተጉዞ የመጣው **የፎርቹን ጋዜጣ ማኔጂንግ ዳይሬክተር (ዋና ሥራአስኪያጅ) አቶ ታምራት ገ/ጊዮርጊስ** ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም ከዚያ በፊት በነበረው ቀን አቶ ታምራት የቢዝነስ ካርዱን ለአቶ ኦባንግ ሰጥቷቸው የነበረ ሲሆን በካርዱ ላይም የነጻ ዜናና ሚዲያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት (Independent News& Media

Plc on the card ሚል በማየታቸው በእርግጥ ነጻ ሚዲያ በኢትዮጵያ ውስጥ አለ ብሎ እንደሚያምን አቶ ታምራትን ይጠይቂታል፡፡ አቶ ታምራት ሲመልስም ‹‹በእርግጥ አለ፤ የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት የተባበሩት መንግሥታትን የሰብዓዊ መብት ጥበቃ መሠረት ያደረገ የሕግ ከለላ በዚህ ጉዳይ ላይ ማድረጉን›› ይገልጻል፡፡ አቶ ኦባንግም ‹‹የፈለከውን ያህል አስደናቂ ሕግ ብታወጣ በተግባር እስካላዋልከው ድረስ ሕጉ ትርጉመቢስ›› መሆኑን ይገልጹለታል፡፡

ሲቀጥሉም በኢትዮጵያ ውስጥ የመለስ አገዛዝ የፈጸመው አሰቃቂ ተግባራት አሁን ያሉበት አመለካከት ላይ እንዲደርሱ እንዳደረጋቸው ከገለጹ በኋላ አቶ መለስ የሥልጣን መንበሩን በተቆጣጠሩበት ወቅት በርካታ ኢትዮጵያውያን አገሪቷን የተሻለች ያደርጓታል የሚል ግምት ነበራቸው በማለት ይመልሱለታል፡፡ አቶ ታምራት ሲቀጥልም ‹‹ታዲያ ምንነበር የምትጠብቀው? ይህ የደገኛ (የአማራ) ፖለቲካ ነው፡፡ ማንም ሥልጣን ያዘ - አማራ ቢሆን ኦሮሞ - ምንም የሚቀየር ነገር የለም›› በማለት ይመልሳል፡፡ አቶ ኦባንግ አጸፋውን ሲመልሱም ‹‹አገራችን አሁን የምትፈልገው የደገኛ ወይም የቆለኛ ፖለቲካ ሳይሆን ፍትሕ፣ እኩልነትና ነጻነት የሰፈነባት ሕዝቧም የፈለገውን መርጦ ሥልጣን ላይ የሚያስቀምጠውና የሚያወርደው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፖለቲካ ነው፡፡ ይህ የማያባራ ዑደት መሰበር አለበት የምንለው ለዚህ ነው፡፡ የጋራ ንቅናቄያችንም ለዚህ ነው የሚታገለው፤ የጎሣ ፖለቲካ ወይም መለስ የዘራውን ዓይነት የዘር ጥላቻ ፈጽሞ አንፈልገውም›› በማለት ሐቁን ይነግሩታል፡፡ አቶ ታምራትን ግን ሙግቱን አላቋረጠም፤ ‹‹እናንተ በውጪ ያላችሁ ለምንድነው መለሰን በሁሉ ነገር የምትወቅሱት? አቶ መለስ በህወሃት ውስጥ በጣም ብሩህ አስተሳሰብ ያላቸው መሪ ናቸው፡፡ ችግሩ ያለው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ራሳቸውን በተገቢው መጠን ማደራጀት ባለመቻላቸው ነው›› በማለት ለአገዛዙና ለአቶ መለስ ያለውን ቁርጠኛ አመለካከት ይናገራል፡፡

አቶ ኦባንግ ሲመልሱም ‹‹መለስ የፈለገውን ያህል ብሩህ አእምሮ ቢኖረው ያንን ሁሉ የተጠቀመው ለጥፋት፣ ለግድያ፣ ለዘር ጥላቻና መከፋፈል›› መሆኑን በመግለጽ ውይይታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ነበር በተከታዩ ቀን በተካሄደው የፓናል ውይይት አቶ ታምራት ገ/ጊዮርጊስ የሚከተለውን ጥያቄ የጠየቀውና አስተያየት የሰጠው፡-

‹‹ኦባንግ የተናገረውን በኢትዮጵያ ውስጥ የፕሬስ ነጻነት የለም የሚለው አስተሳሰብ ፈጽሞ ውሸት ነው፡፡ ሆኖም አሁን በዚህ ጉዳይ ላይ ላተኩር አልሻም፤ ከዚያ ይልቅ ግን የመሬት ሊዙን በተመለከተ ነዋሪዎች ከቦታቸው ተፈናቅለዋል በማለት ኦባንግ የተናገረውን ፈጽሞ የተሳሳተ አስተሳሰብ ስለሆነ ልቃወመው እፈልጋለሁ፡፡ በመጀመሪያ በኢትዮጵያ የመሬት ነጠቃ አይደለም እየተካሄደ ያለው፤ ከቦታቸው የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ፈጽሞ የሉም፡፡ እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ደሃ አገር ነች፤ ሰዎች ኢትዮጵያ ራሷን እንድታሻሽል ከፈለጉ ባለሃብቶች ወደአገሪቷ በመምጣት መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ሊፈቀድላቸው ይገባል፡፡››



ለዚህ ከነጻ ጋዜጠኛ ሳይሆን ከአገዛዙ ካድሬ ለተሰጠ የሚመስል አስተያየት አቶ ኦባንግ አጸፋውን መልሰዋል፡፡ በቅድሚያ ያደረጉት ጆን ቪዳል የተባለው የጋርዲያን ጋዜጣ የአካባቢጥበቃ አርታኢ ያዘጋጀውን አጭር ቪዲዮ ጉባዔተኛው እንዲመለከት በማድረግ ነበር፡፡ (ከዚህ በፊት ላልተለመከታችሁ አንባቢያን በሙሉ ይህንን ድንቅ ቪዲዮ እንድትመለከቱ እንጋብዛችኋለን፡፡ http://www.guardian.co.uk/world/2011/mar/21/ethiopia-centre-global-farmland-rush?CMP=twt_gu)
ቪዲዮው የሚያሳየው የሕንዱ ካራቱሪና የአላሙዲ ሳውዲ ስታር ኩባንያዎች መሬት ከተረከቡ በኋላ ነዋሪዎች ከቦታቸው እንዴት እንደተፈናቀሉና ዛፍ ሥር እስከመተኛት እንደደረሱ የሚዘግብ ነው፡፡ ነዋሪዎቹ ምን እየደረሰባቸው እንደሆነ ሲጠየቁ ከፍርሃት የተነሳ ለመናገር እንደማይደፍሩ ሁሉ የሚያሳይ ነው፡፡ ቪዲዮው ከታየ በኋላ አቶ ኦባንግ ‹‹የነጻ ጋዜጣ አታሚውን›› ታምራት የሚከተለውን ጥያቄ ይጠይቁታል፡- ‹‹እዚህ ጋር አንድ ሰው እየዋሸ ነው፡፡ ወይ አንተ ወይም ይህንን ቪዲዮ ያዘጋጀው ጋዜጠኛ፡፡›› ሲቀጥሉም ‹‹እነዚህ እዚህ ቪዲዮ ላይ የታዩት ግለሰቦች ከሱዳን ወይም ከኬኒያ የመጡ አይደሉም፡፡ አንተ ራስህ አይተሃቸዋል፤ ምናልባት በሌሎች ክልሎች የሚካሄደውን

***በማምታታት ልታቀርብ ትሞክር ይሆናል፡፡ እነዚህ እዚህ ቪዲዮ ላይ ያየሃቸው ሰዎች ግን የጋምቤላ ሰዎች ናቸው - እኔ በግል አውቃቸዋለሁ፤ ከእነርሱ ጋር በየቀኑ እገናኛለሁ፤ እየደረሰባቸው ያለውን ሁኔታ በቅርብ እከታተላለሁ፡፡ ስለዚህ ያቀረብከው ማስተባበያ የራስህ ፈጠራ ለመሆኑ ማስረጃው ይኸው ነው፡፡ ግን እንደው ለመሆኑ አንተ ነጻ ጋዜጠኛ ነኝ እያልክ  የፈለከውን እየጻፍክ እስካሁን ምንም ሳይደርስብህ ለምንድነው በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ባለሙያ ጋዜጠኞች ዕድሜ ልካቸውን ለእስር፣ እንግልት፣ ስደትና ሞት የተጋለጡት?***›› በማለት አቶ ኦባንግ አስተያየታቸውን በጥያቄ ይደመድማሉ፡፡ (ይህ ሁሉ የሆነው የአውራምባው ውብሸት ታዬና የፍትሕ ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ በአሸባሪነት በታሰሩበት ሰሞን መሆኑን አንባቢ ልብ ይሏል፡፡) **የፓናል ውይይቱ አስባባሪም ከአቶ ኦባንግ ለተሰነዘረው ጥያቄውና አስተያየት የአጸፋ መልስ እንዲሰጥ ለአቶ ታምራት ዕድሉን ቢሰጡትም *‹‹መልስ የለኝም››* ከማለት ሌላ የሚመልሰው አልነበረም፡፡**

ምንም እንኳን የህወሃት/ኢአዴግ አገዛዝ ጋዜጠኞችን በማስፈራራት፣ በማሰር፣ በማንገላታት ወዘተ ከተግባራቸው ሊያፈናቅላቸው ቢሞክርም አሁንም ግን እነርሱ እውነትን ከመናገር ቅንጣት ታህል ወደኋላ አይሉም፡፡ ባላፈው ሳምንት ብቻ የ“አዲስ ወሬ” ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር ጽንኤል ኃይሉ በደኅንነት ሰዎች መታገቱን፣ መመርመሩንና፣ መመታቱን አዲስ ነገር ዘግቧል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን **‹‹በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ጋዜጣውን እንድትዘጋ››** የሚል ጥብቅ ማስጠንቀቂያ እንደተነገረውና ቢሮው መበርበሩን፣ የኢሜይል (የፖዳቤ) መልዕክቶቹ መነበባቸውንና ወደማያውቀው ስፍራ ተወስዶ በውጭ አገር ካሉ ተቃዋሚዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ምን እንደሆነ ሲመረመር እንዳደረ አዲስ ነገር ጨምሮ ዘግቧል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፤ ጋዜጠኛው በአሸባሪነት የታሰረችበት የፍትሕ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ መለስ ከሥልጣን እንዲለቁ አምርሮ መጠየቁን አዲስ ነገር ጨምሮ ዘግቧል፡፡ ጋዜጠኛው ከጻፋቸው መካከል አቶ መለስ ተቀበሉትም አልተቀበሉት በእርሳቸው አመራር **‹‹ሀገር እና ትውልድ እየጠፋ ነው››** ካለ በኋላ ሲቀጥል **‹‹እኛ ግን እንዲያውም ንገረኝ ካሉኝ ከአልሸባብና ከአልቃይዳ ይልቅ የሚያሰጋን የኑሮ ውድነቱ ነው፡፡ በፈንጅ እናልቃለን ከሚለው ይልቅ በረሃብ አንሞት ይሆን? ብሎ የሚሰጋው ይበልጣል››** ይላል፡፡ በማስከተልም አቶ መለስ አሁንም **‹‹‘ንብረቴ መጽሐፎቼ ናቸው’ እንደማይሉን እርግጠኛ ነኝ፡፡ ይሄ ለተረት እንጂ ለፕሮፓጋንዳም አይጠቅምም››** ይልቁንም **‹‹ለ20 ዓመት በጉልበት ስልጣን ላይ ቆይተዋል፤ ቅር ቢለንም ይቅር እንልዎታለን፡፡ አሁን ግን በቃዎት፡፡ …አመራርዎ ያደረሰብንን ችግር ደጋግሞ መዘርዘሩ ‘የሞኝ ዘፈን…’ ስለሚሆንብኝ ቢበቃኝ መልካም ነው፡፡እናም በአሁኑ ወቅት ያለው የአገራችን ችግር እርሶ በአመራር ላይ እስካሉ ድረስ ሊፈታ የሚችል አይደለምና ለሀገሪቷና ለ80 ሚሊዮን ሕዝብ ሲሉ ሥልጣንዎን ይልቀቁ፡፡”** በማለት የጀግና መልዕክቱን በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም አስተላልፏል፡፡ እነዚህ ደፋርና ጀግና ጋዜጠኞች የፈለገው ቢደርስባቸውም ላለፉት 20 ዓመታት ያለማቋረጥ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝን አጥብቀው የተቃወሙ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆችና ባለውለታዎች ናቸው፡፡

አሁን ከሚታዩት አጠቃላይ ሁኔታዎች አንጻር የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ አክትሞለታል፡፡ ሆኖም እንደ ታምራት ገ/ጊዮርጊስ ዓይነቱ የሥርዓቱ አቀንቃኞች አሁንም የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ተግባር በየቦታው ሲፈጽሙ ይታያሉ፡፡ የጋራ ንቅናቄያችን ከእንግዲህ ወዲህ ህወሃት/ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውን መከራ እንደ ‹‹ሞኝ ዘፈን›› ሲያሳውቅ የሚኖር አለመሆኑን ሁሉም ወገን ሊያውቀው ይገባል፡፡ ከእንግዲህ ያለው አንዱና ብቸኛ አማራጭ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከያዘው ሥልጣን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ መልቀቅ ነው፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት የጋራ ንቅናቄያችን በሁሉም አቅጣጫ እየሠራ መሆኑን እየገለጽን የህወሃት/ኢህአዴግን አገዛዝ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ስትደግፉ የነበራችሁ ይህንን እየሞተ ያለ አገዛዝ መደገፋችሁን ትታችሁ ከሕዝባዊው ትግል ጋር እንድትቀላቀሉ ጥሪ እናቀርባለን፡፡ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ‹‹**ከዘር ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ የሚሰጥባትን አዲሲቱን ኢትዮጵያ**›› ለመመሥረት በሚደረገው የመጨረሻ ሰላማዊ ፍልሚያ በተጠንቀቅ ቁሙ፡፡

ፈጣሪ ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ሁላችንም በአንድ ልብና በአንድ ሃሳብ ያነሳሳን፡፡ ከጥላቻና ከበቀል በጸዳ መልኩ በፍትሕ፣ በእኩልነት እና በነጻነት ምሰሶዎች ላይ ለምትመሠረተው ‹‹አዲሲቷ ኢትዮጵያ›› ሁላችንም በአንድነት እንቁም፡፡

---

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

